

# ስድስተኛው የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን መስከረም 12 ቀን 2006 ዓ.ም. በጣሊያን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ በርካታ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በድምቀት ተከበረ!



ስድስተኛው የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን መስከረም 12 ቀን 2006 ዓ.ም. በሮም ሚሲዮን በርካታ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል፡፡

በእለቱ **«ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሃነታችን፣ የአንድነታችንና የሕዳሴያችን መገለጫ ነው!»** የሚለው የበአሉ መሪ ቃል መሠረት በማድረግ ክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ ለተሰብሳቢው ማኅበረሰብ ንግግር አሰምተዋል፡፡ ክቡር አምባሳደሩ በንግግራቸው የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማው ይዘት ትርጉምና ከሕገ-መግሥታችን መሠረታዊ ምሰሶዎች ጋር ያለው ትስስር፣ የተጀመረው ፀረ-ድህነት ትግል እያሳየ ያለው አመርቂ ውጤትና ይኸንኑ በትውልድ ቅብብሎሽ ለማስቀጠል የወጣቶችና የሴቶች የማይተካ ሚና እንዳላቸው፣ በአሁኑ ወቅት በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ስልጣን ለመጨበጥ እየተሯሯጡ ያሉት ኃይሎች አፍራሽ ተልዕኮ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሕጋዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሊታገለውና ሕልማቸውን ሊያከሽፍ እንደሚገባ፣ በሰንደቅ ዓላማው ሥር በመሰለፍ አገራችን በታሪኳ የምትታወቅበት የሕዝባችን የሃይማኖቶች መቻቻል እሴት መጠበቅና ማጉልበት እንደሚያስፈልግ፣ እንዲሁም ዲያስፖራው በአገሩ ልማት በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በመሳተፍ ራሱን ጠቅሞ አገሩንም መጥቀም እንደሚችል አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም በሮም አካባቢ ከተቋቋሙት የአማራ ልማት ማኅበር፣ የትግራይ ልማት ማኅበር፣ የሴቶችና የወጣቶች ተወካዮች እለቱን አስመልክተው

የሰንደቅ ዓላማ ትርጉምና ጠቃሚነት ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል።

በመጨረሻም ተሳታፊዎች በጋራ ብሔራዊ መዝሙር በመዘመር፣ ለአገራችን ልማትና እድገት የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ ቃለ-መሃላ በማድረግና ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማውን ከፍ አድርገው በማውለብለብ በአሉን በከፍተኛ ድምቀት አክብረዋል።








